ይህ ሕግ የኢሚግሬሽን ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን በመተግበሪያ ላይ የተመሰረቱ ሠራተኞችን ይከላከላል።

የተካተቱ የኔትወርክ ኩባንያዎች ይህንን ሕግ ማክበር አለባቸው። የበቀል እርምጃ ህገ ወጥ ነው። ከጃኑዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

Seattle Office of Labor Standards

# App-Based Worker Deactivation Rights (ABWDR) Ordinance (በመተግበሪያ ላይ የተመሠረቱ ሠራተኞች የቅጥር ማቋረጥ መብቶች ድንጋጌ (ABWDR) ድንጋጌ)

# የ SMC 8.40 የመብቶች ማስታወቂያ

## ከጃኑዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል

## እርስዎ እንደዚ ከሆኑ የሚሸፈኑ ይሆናል፡-

- ቢያንስ 25% የሚሆኑት የተጠናቀቁ ቅናሾችዎ እና/ወይም ከማሰናበቱ በፊት ባሉት 180 ቀናት ውስጥ በምክንያት የሰረዙት ቅናሾች በሲያትል ውስጥ ለተሸፈነው የኔትወርክ ኩባንያ አገልግሎቶችን ማቅረብን ያካተቱ ናቸው፤ ወይም
- ቅጥርዎ የተቋዋረጠው በሲያትል ለአንድ የተሸፈነ የኔትወርክ ኩባንያ አገልግሎት ሲሰጡ በነበረበት ወቅት ከተከሰተው ክስተት ወይም ክስተቶች ጋር በተያያዘ ነው።

በመተግበሪያ ላይ የተመሰረቱ መድረኮችን ለሥራ የሚጠቀሙ ሁሉም ሠራተኞች በዚህ ሕግ አይሸፈኑም። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እዚህ ጋር ይቃኙ፡-

https://www.seattle.gov/laborstandards/ordinances/app-based-worker-ordinances/app-based-worker-deactivation-rights-ordinance

አፕሊኬሽን የሚጠቀሙ የሲያትል ሠራተኞችን በሚመለከት ሕግጋቶቹ የትራንስፖርት ኔትወርክ ኩባንያ (የራይድ ሼር) አሽከርካሪዎችን አይሸፍኑም።

## የተሸፈነ መተግበሪያ ላይ የተመሠረተ ሠራተኛ እንደመሆንዎ መጠን የሚከተሉትን የማድረግ መብት አለዎት፡-

- ምን ዓይነት እርምጃዎች ወደ ቅጥር ማቋረጥ ሊያመሩ እንደሚችሉ እና ቅጥር ማቋረጥን ለመቃወም የሚያስችል አሠራር የሚገልጽ የቅጥር ማቋረጥ ፖሊሲ ፍትሃዊ ማስታወቂያ ይቀበሉ።
  - የቅጥር ማቋረጥን ፖሊሲ ከኩባንያው አሠራር ጋር በተመጣጣኝ ሁኔታ የተያያዘ መሆን አለበት።
- የኔትወርክ ኩባንያው ውስጣዊ የቅጥር ማቋረጥ አቤቱታ አሰራር በኩል የቅጥርዎን መቋረጥ ጥያቄ ያቅርቡ፣ ወደ ቅጥር መቋረጡ የሚያመራው ክስተት የትም ቢከሰት።
- የ 14 ቀናት ማስጠንቀቂያ ቅጥርዎ ከመቋረጡ በፊት ይሰጥዎታል፣ ከባድ ጥፋት ወይም በሕግ ከልተጠየቀ በስተቀር በዚህ ሁኔታ ኩባንያዎች ወዲያውኑ ቅጥርዎን ሊያቋርጡ ይችላሉ።
  - ማስታወቂያው የኩባንያውን ፖሊሲ የጣሰውን የተወሰነ ክስተት(ቶች) ጨምሮ ቅጥርዎን ለማቋረጡ ምክንያቱን(ዎቹን) እና የኔትዎርክ ኩባንያው የእርስዎን ቅጥር ለማቋረጥ ውሳኔውን ለመስጠት የተመሠረተባቸውን እና ያሰቧቸውን ሁሉንም መዝገቦች ማቅረብ አለበት።

## የኔትወርክ ኩባንያዎች፡-

- አድልዎ ለማድረግ የታሰበ ወይም የታሰበን ቅጥር ማቋረጥን ጨምሮ “ያልተረጋገጠ” የቅጥር ማቋረት እርስዎ ላይ ሊፈጽሙ አይችሉም።
- የእርስዎን ቅጥር ከማቋረጡ በፊት የኩባንያውን ፖሊሲዎች ጥሰዋል የሚሉ ክሶችን መመርመር አለበት እና እርስዎ ፖሊሲውን እንደጣሱ ማሳየት አለበት።
- በቅጥር ማቋርጥ ዙሪያ ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን እና ቅጣቶችን በተከታታይ መተግበር አለበት።
- የእርስዎን ቅጥር ማቋረጥ የሚችሉት ከጣሱት ጉዳዩ ጋር በተያያዘ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው እና የሥራዎን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

- ህጎችን፣ ደንቦችን ለማክበር ወይም ከባድ ጥፋት በመፈጸምዎ ምክንያት ወዲያውኑ ቅጥርዎን ሊያቋርጡት ይችላሉ።
- በዚህ ድንጋጌ ስር የተካተቱ መሆንዎን ወይም ወይም አለመሆኑን ለመረዳት የሚረዳ ስርዓት እንዲፈጥሩ ይጠየቃሉ።
- ይህንን የመብቶች ማስታወቂያ በእንግሊዝኛ እና እርስዎ በሚያውቁት ዋና ቋንቋ በስማርትፎን መተግበሪያ፣ በኢሜይል ወይም በመስመር ላይ የድረገጽ ፖርታል በኩል ለእርስዎ መስጠት አለበት።

## መብቶችዎን ይወቁ፡-

### የበቀል እርምጃ የተከለከለ ነው

ከላይ የተጠቀሱትን መብቶች በመጠቀም ወይም በተግባር ላይ በማዋል ምክንያት ከበቀል (ከአሉታዊ እርምጃ) የመጠበቅ መብት አለዎት።

### ቅሬታ የማቅረብ መብት

በኩባንያው ውስጣዊ አሰራሮች አማካኝነት የቅጥር መቋረጥዎን በመቃወም ለ Office of Labor Standards (OLS፣ በሠራተኛ ደረጃዎች ቢሮ) ቅሬታ የማቅረብ ወይም ክስ የመመስረት መብት አለዎት።

**ከጁን 1፣ 2027 በፊት OLS በዚህ ሕግ ሕግ ውስጥ የተወሰኑ መብቶችን ለማስፈጸም**

**ውስን ሥልጣን ይኖረዋል። ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት እዚህ ጋር ይቃኙ፡-**

https://www.seattle.gov/laborstandards/ordinances/app-based-worker-ordinances/app-based-worker-deactivation-rights-ordinance

ሠራተኞች OLS ገና ማስከበር የማይችላቸውን መብቶች ለማሟላት ሌሎች መንገዶችን መፈለግ ይችላሉ።

## OLSን ያነጋግሩ፦

### የኔትወርክ ኩባንያዎች
የቴክኒክ ድጋፍ እና/ወይም ስልጠና ማግኘት

### በመተግበሪያ ላይ የተመሰረቱ ሠራተኞች
ለ OLS ቅሬታ ወይም ለፍርድ ቤት ክስ ያቅርቡ

# 206-256-5297

**www.seattle.gov/laborstandards**

**Seattle** Office of Labor Standards


810 THIRD AVE, SUITE 375
SEATTLE, WA 98104
ሰዓታት፦ 8:00 AM– 4:00 PM (ከሰኞ–አርብ)
LABORSTANDARDS@SEATTLE.GOV


Office of Labor Standards (የሠራተኛ ደረጃዎች ጽሕፈት ቤት) ተልዕኮ የሠራተኛ ደረጃዎችን በማስተዋል ማህበረሰብ እና የንግድ ተሳትፎ፣ ስትራቴጂካዊ አፈጻጸም እና የፈጠራ ፖሊሲ ልማት፣ በዘር እና በማህበራዊ ፍትህ ቁርጠኝነት በኩል ማራመድ ነው።

የሠራተኛ ደረጃዎች ጽ/ቤት ለአካል ጉዳተኞች የጽሁፍ ትርጉሞችን፣ የቃላት ትርጉሞችን እና አቅራቦቶችን ይሰጣል።